# ፀረ ሙስና

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅፅ 1 ቁጥር 2 ነሐሴ 2014 ዓ.ም

# የኮሚሽኑ ህንፃ ዕድሳት ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዚህ በፊት ሲገለገልበት የነበረውን ህንፃ እንደ አዲስ በማደስ ዘመናዊ፣ ለስራ ምቹና ቀልጣፋ አድርጎ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ህንፃው 76 ሚሊዮን በር የፈጀ ሲሆን 65 ሚሊዮን ብር በመንግስት በጀት ተመድቦለት ቀሪው 11 ሚሊዮን ብር ደግሞ የአሰራር ስርአቱን አዘምኖ ወደ ዲጂታላይዜሽን ሲስተም እንዲገባ የዓለም ባንክ ድጋፍ አድርጎለታል፡፡ በዚህም ዕድሳቱ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በስፋት ለመጠቀም እና አገልግሎት አሰጣጡን ወረቀት አልባ በማድረግ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚሠጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡ ተያይዞም ምቹ እና ዘመናዊ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘ ቢሮ በማድረግ ለሠራተኛው ምቹ የሆነ የሥራ አካባቢ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ ኮሚሽኑ ከዚህ በፊት ተከራይቶ ይጠቀምበት ለነበረው ህንፃ በዓመት ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ያወጣ የነበረውን ወጪ ማስቀረት ተችሏል፡፡





## ዐቃቤ ህግ ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ በተያዘው የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ላይ ክስ መሰረተ

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

ተከሳሽ በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ውስጥ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ እና በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የዋና ስራ አስፈጻሚ አማካሪ እና የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት ጉቦ በመጠየቅና በመቀበል ከባድ የሙስና ወንጀል በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

የዐቃቤ ህግ ክስ እንደሚያስረዳው 1ኛ ተከሳሽ አቶ ፍቃዱ መገናሳ ሽብሩ በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤቶች ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ እና 2ኛ ተከሳሽ አቶ ደስታ ንጋቱ ሀይለማርቆስ የቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ በስራ ኃላፊነታቸው ማድረግ የማይገባቸውን ለማድረግ በማሰብ የግል

ዐቃቤ ህግ... ወደ ገፅ 2 የዞረ

## አገር አቀፍ የሙስና መከላከል ትስስር ጉባዔ ተካሄደ



የፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2015 በጀት ዓመት መሪ ዕቅድን ለማሳካት ከክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ሀገር ዓቀፍ የሙስና መከላከል ትስስር ጉባዔ በ23/12/2014 ዓ.ም በኮሚሽኑ ዋና ጽ/ቤት አካሂዷል፡፡

በዕለቱ የዝግጅት ምዕራፍ ዘርፍ ተኮር የአቅም ግንባታ ሥልጠና በቅንጅት ማከናወን፣ የዲጂታል

አገር አቀፍ.... ወደ ገፅ 2 የዞረ

## ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ተቋሙን የማዘመን ተግባራትን አከናወነ



የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽኑን በዲጂታል የአሠራር ስርዓት ለማዘመን በ2014 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በኮሚሽኑ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የስራ ክፍል ተወካይ አቶ ሙሉጌታ ድንቁ ገለፃ በ2014 በጀት ዓመት ተቋሙን በዲጂታል አሠራር ሥርዓት ለማዘመን ታቅዶ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ዘመናዊ የኔትወርክ ዝርጋታ በማከናወን ሀብትን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ በቴክኖሎጂ በመታገዝ መጠቀም እንዲቻል ተደርጓል፡፡የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ የመስመር ላይ ምዝገባ/Online Registration/ Disclosure and asset registration system (DARS) ሶፍትዌርን በማስለማት እና ለሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ሥልጠና በመስጠት ሥራ እንዲጀምር የተደረገ ሲሆን IFMS ቴክኖሎጂን በተመለከተ ለአጠቃቀም እንዲመች ተደርጎ ፍጥነቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ የሥነ-ምግባር ግንባታ፣ የሙስና መከላከልና የሙስና መረጃ ማመንጨት ስራዎች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን የመረጃ ተደራሽነት ስርዓትን በመዘርጋትና ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ የኮሚሽኑን የዌብ ሳይት፣ የቴሌግራም፣ የዩቲዩብ፣ የፌስቡክ እና የትዊተር ገፆችን በመክፈት ኮሚሽኑ ሶሻል ሚዲያን በስፋት እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የፌስቡክ ገፁ እውቅና /blue badge/ እንዲያገኝ በማድረግ ግንዛቤ የሚፈጥሩ የሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል መልዕክቶችንና መረጃዎችን ለሕዝብ ተደራሽ የማድረግ ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ የሶሻል ሚዲያ ፍጥነትም በፊት ከነበረበት 38MB ወደ 1 GB እንዲያድግ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም 300 MB backup እንዲይዝ መደረጉን አቶ ሙሉጌታ ገልፀዋል፡፡

National Ethics and Integrity Portal ሥራ ለመጀመር ዌብሳይት የማልማት ስራ ያስጀመረ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የኮሚሽኑን አገራዊ አቅም ግንባታ ሥልጠና ማጎልበቻ አካዳሚ/ማዕከል 20% መሰረተ ልማት ለማሟላት ታቅዶ የOnline Training ለመስጠት የሚያስችል ስቱዲዮ (Vertual Training Room) ግንባታ ከመንግስት ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር ውል በመፈፀም የግንባታ ስራው የተጠናቀቀ መሆኑን ገልፀው በቀጣይ ሥልጠናውን ለመስጠት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ግብአቶች ለሟሟላት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመሠራት ላይ እንደሚገኝም አቶ ሙሉጌታ አያይዘው ጠቁመዋል፡፡ በሌላ መልኩ ኮሚሽኑ እየዘረጋ ያለውን የዲጂታላይዜሽን ሥራ ተግባራዊ ለማድረግ የአመራሩ እና የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር መሠረታዊ የአይሲቲ ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ኮሚሽኑ እየዘረጋ ያለውን በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥ በICT እና የዲጂታል አሠራር ሥርዓት አጠቃቀም መመሪያ የተደገፈ እንዲሆን ለማድረግ ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በሂደት ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ዐቃቤ ሕግ በአቶ ምትኩ ካሣ እና ግብረ-አበሮቹ ላይ የመሠረተውን የክስ ዝርዝር አቀረበ



ዐቃቤ ሕግ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩት አቶ ምትኩ ካሣ እና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ግብረ-አበሮቹ ላይ የመሠረተውን የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ክስ ዝርዝር በዛሬው ዕለት አቅርቧል።

ተከሳሾች 1ኛ አቶ ምትኩ ካሳ ጉትሌ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩ፣ 2ኛ. አቶ አራጋው ለማ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የፋይናንስ ዳይሬክተር፣ 3ኛ አቶ የማነ ወ/ማሪያም የኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንደ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን ዋና ዳይሬክተር የነበሩ፣ 4ኛ ዶ/ር ዮናስ ወ/ትንሳይ የኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንደ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ 5ኛ አቶ ደመወዝ ኃይሉ ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንደ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን የፋይናንስ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ 6ኛ ወ/ሮ ሶፊያ ጀማል ሰላሙ የ1ኛ ተከሳሽ የትዳር አጋር 7ኛ ወ/ሮ ሚልካ ምትኩ ካሳ የምትኩ ካሳ ልጅ፣ 8ኛ አቶ ኢያሱ ምትኩ ካሳ የምትኩ ካሳ ልጅ፣ 9ኛ አቶ መብራቱ አሰፋ የኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንደ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን የመጋዘን ንብረት መዝጋቢ/ሰቶር ኦፊሰር፣ 10ኛ አቶ ገ/ሚካኤል አብረሓ የኤልሻዳይ አሶሴሽን ሰቶር ኦፊሰር እና የንብረት ክፍል ሠራተኛ፣ 11ኛ አቶ ዮሐንስ በላይ ተድላ፣ 12ኛ አቶ ጌቱ አስራት እና 13ኛ ወ/ሮ ሕይወት ከበደ ናቸው።

የዐቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር እንደሚያሳየው 1ኛ ተከሳሽ አቶ ምትኩ ካሣ እና ሌሎች ተከሳሾች ሕገ-ወጥ ጥቅም ያገኙ ወይም ያስገኙ እና በዚሁም ልክ በመንግሥት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆኑ በዋና እና በልዩ ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት ሥልጣንን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰዋል።

በተጨማሪም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል በ1ኛ፣ 3ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ፣ 11ኛ፣ 12ኛ፣ እና 13ኛ ተከሳሾች ክስ የተመሠረተባቸው ሲሆን በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የውጭ ምንዛሬ ይዞ መገኘት ወንጀልን ጨምሮ 1ኛ ተከሳሽ ላይ 4 ተደራራቢ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ተመሥርቶባቸዋል።

ነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም በነበረው ችሎት 1ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች አቶ ምትኩ ካሣ እና ልጃቸው ከሁለት ጠበቆቻቸው ጋር እና 11ኛ ተከሳሽ ችሎት ቀርበው ማንነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ክሱ ተነቦላቸዋል።

8ኛ ተከሳሽ ኢያሱ ምትኩ ካሣ የተከሰሱበት አንቀፅ ዋስትና የማይከለክላቸው በመሆኑ ጉዳያቸውን ከውጪ ሆነው እንዲከታተሉ በጠበቆቻቸው የተጠየቀ ሲሆን ዐቃቤ ሕግም ተቃውሞ ባለማቅረቡ ፍርድ ቤቱ 8ኛ ተከሳሽ በ50 ሺህ ብር ዋስትና ከእስር እንዲፈቱ ፈቅዶላቸዋል።

አቶ ምትኩ ካሣ እና 11 ተከሳሾች የክስ መቃወሚያቸውን እስከ መስከረም 10 ዐቃቤ ሕግ በመቃወሚያው ላይ እስከ መስከረም 20 አስተያየት እንዲሰጥበት በማለት በዚህም ላይ ብይን ለመስጠት እና ሌሎች ተከሳሾች ሲቀርቡ ለማየት ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠት ተከሳሾቹ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ እና የፌደራል ፖሊስ ሌሎች ተከሳሾችን አፈላልጎ እንዲያቀርብ መታዘዙን ከፍትሕ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ኮሚሽኑ በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከሠራተኞች ጋር ውይይት አካሄደ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ በ26/12/14ዓ.ም ከኮሚሽኑ ሰራተኞች ጋር ውይይት አካሄደ፡፡

በዕለቱ ሀገራችን የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ ያብራሩት የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ እንደገለፁት የሠላም ዋጋው በምንም ሊተምን የማይችል እና መንግስትም ምንጊዜም ቢሆን ለሰላም ዝግጁ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ ኮሚሽነሩ አያይዘውም ሀገራችን አሁን ያለችበትን ፈታኝ ሁኔታ ለማለፍ የመላው ህዝብ የጋራ ርብርብ እንደሚጠይቅ አስታውሰው በዚህ ሂደትም የኮሚሽኑ ሠራተኞችም ሀገራዊ ሚናቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡

አስተያየት የሰጡ የውይይቱ ተሳታፊዎች እንደተናገሩት ያለን አንድ ሀገር መሆኑን ጠቅሰው ይህችን ሀገራችንን ለመጠበቅ የጋራ አብሮነታችንን እንደ ከዚህ ቀደሙ አጠናክሮ መቀጠል አለብን ያሉ ሲሆን በተጨማሪም ሀገራችን ያላት የጦርነት ታሪክ ማስቀረት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡





## ዐቃቤ ህግ...

ከገፅ 1 የቀጠለ

ተበዳይ ወ/ሮ እየሩሳሌም ሰይድ ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ የውሃ እና መብራት እየከፈለች በሰነድ አልባ ይዞታ የምትኖርበት በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ መኖሪያ ቤቷን በተመለከተ 1ኛ ተከሳሽ የቤቶች ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ወደግል ተበዳይ ስልክ ደውሎ ”ቤትሽ የቀበሌ ቤት ውስጥ ስለሚገኝ ቤቱ እና የቤቱ ቁልፍ ለመንግስት አስረክቢ የማታስረክቢ ከሆነ በፖሊስ እና በደንብ ማስከበር እንድትወጪ እናደርጋለን“ ብሎ ሲያስፈራራት የግል ተበዳይም ነገሩን ለማጣራት ስትሞክር ለጊዜው ያልተያዘው ተከሳሾች ያዘጋጁት አንሙት የሚባል ግለሰብ ተከሳሾቹ 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺ) ብር እንደሚፈልጉ ሲነግራት የግል ተበዳይ ይህንን ያህል ገንዘብ መክፍል እንደማትችል ስትነግረው እሱም ከተከሳሾቹ ጋር እንድትገናኝ በነገራት መሰረት የግል ተበዳይ ሀምሌ 01 ቀን 2014 ዓ/ም ከጠዋቱ 4፡00 በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ልዩ ቦታው ሚስዮን ትምህርት ቤት አካባቢ 2ኛ ተከሳሽን በአካል አግኝታ ስታናግረው “ቤትሽን ህጋዊ ለማድረግ ከፈለግሽ አንሙት የነገረሽን ገንዘብ ለምን አትከፍይም?“ ሲላት እሷም ገንዘቡ መብዛቱን ስትገልፅለት “ይሄ ገንዘብ እኮ እስከ ደንብ ማስከበር አባላት ነው የሚከፋፈለው ያንቺ ሀሳብ ስንት ነው?“ ብሎ በመጠየቅ እና በመደራደር በ 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ብር ይስማማሉ፤ በመጨረሻም የግል ተበዳይ ለመክፈል የተስማማችውን 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺ) ብር ለመቀበል ሃምሌ 12 ቀን 2014 ዓ/ም ከቀኑ 5፡30 ሲሆን

1ኛ ተከሳሽ በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ልዩ ቦታው ጌቱ ኮሜርሻል አካባቢ በመሄድ ገንዘቡን በመቀበል ሱቅ አስቀምጦ ሲሄድ እጅ ከፍንጅ የተያዘ በመሆኑ ሁለቱም ተከሳሾች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) ሀ እና የሙስና ወንጀሎች ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 10(2) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት ጉቦ መጠየቅና መቀበል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

ተከሳሾችም በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ቀርበው የክስ መቃወሚያቸውን ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የተከሳሾችን መቃወሚያ እና የዐቃቤ ህግን አስተያየት መርምሮ ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮ እንደተሰጣቸው ከፍትህ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

ጉቦ መቀበል ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነት ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለራሱም ይሁን ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

## አገር አቀፍ....

ከገፅ 1 የቀጠለ

ሀብት ምዝገባ አሠራርን በመጠቀም ጥራትና ተገቢነት ያለውን መረጃ ማመንጨት እና ሙስና መከላከል፣ ሀገር ዓቀፍ የሙስና መከላከል ጥምረት የትኩረት ጉዳዮች ማድረግ ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡

በውይይቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ እንደገለፁት በ2015 በጀት ዓመት ሙስናን የመከላከል ሥራው መረጃ ላይ የተመሰረተና ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣ መሆን እንዳለበት ጠቁመው በዚህም ሙስናን በተለመደው አካሄድ መከላከል ባለመቻሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጉዳቶችን እያስከተለ እንደሚገኝና ይህንንም ለመከላከል ደግሞ የክልል ኮሚሽነሮች ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል፡፡

ኮሚሽኑ በዚህ ዓመት ሙስናን በተደራጀ መልኩ ለመከላከል ጥምረት የመሰረተ ሲሆን ከዚህ በፊት የነበረውን የተበታተኑ ስራዎችን ወደ አንድ በማምጣት ውጤት ያለው ስራ እንዲሰራ ያደርጋል፡፡ ሌላው በሙስና ላይ የህብረተሰቡን አመለካከት ለመቀየር በሰፊው የሥ-ነምግባር ሥልጠና የሚሰጥ ሲሆን መረጃን በተሻለ መልኩ በማደራጀት ቀልጣፋ አገልግሎትን በመስጠት የመረጃ ፍሰቱን በማሳለጥ ሙስና የመከላከል ሥራውን ማከናወን የኮሚሽኑ አንዱ ዕቅድ ነው፡፡

እንደ ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ ገለፃ ሀገሪቱ በምትፈልገው ደረጃ ሙስናን የሚከላከሉ የፌደራልም ይሁን የክልል የበቁ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አሉ ለማለት የማያስደፍር ሲሆን የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ነፃ፣ ገለልተኛና ዲሞክራቲክ የሆኑ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችን መፍጠር ቀጣይ የኮሚሽኑ የትኩረት አቅጣጫ ነው፤ ክልሎችም ከዚህ አኳያ እንደየ መንግስታቸው ተጨባጭ ሁኔታ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ገልፀዋል፡፡ ኮሚሽነሩ አያይዘውም ዘርፍ ተኮር የሆነ ስልጠና በሀገሪቱ ለሚገኙ ከ6,000 በላይ ለሆኑ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚሰጥ ሲሆን በጀቱና አሰልጣኝ ምደባው በኮሚሽኑ እንደሚደረግ ጠቁመዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት የከተማ መሬት አስተዳደር፣ ትልልቅ የመንግሥት ፕሮጀክቶች፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ ገቢዎችና ጉምሩክ፣ ለመንግስት ፕሮጀክቶች በድጋፍ የሚመጡ ገንዘብ አጠቃቀም፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ኮሚሽኑ ሙስናን ለመከላከል ካስቀመጣቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ ይገኙበታል፡፡

# ርዕሰ-አንቀፅ

በሀገራችን ሙስና እና ብልሹ አሠራር የዕድገትና የሰላም ተግዳሮት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን የሠላም እና የእድገት ፀር የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሠራር ችግር በየደረጃው በእውቀትና በመረጃ ላይ ተመስርቶ መታገልና የአገራችንን የብልፅግና ጉዞ ማረጋገጥ የወቅቱ ቁልፍ አጀንዳ ነው፡፡ መንግስት ከዚህ አንፃር በሌብነት ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ እንዳለበት አቋሙንና አቅጣጫውን በተደጋጋሚ ግልፅ አድርጓል፡፡

ኮሚሽናችን የሥነ-ምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ትግል በአገር ደረጃ የማስተባበር ከባድ ተልዕኮ ያለው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በ2014 ዓ.ም ሠፋፊ የሪፎርም ሥራዎችን ማለትም ተቋማዊ አቅም እና ብቃት ከማረጋገጥ አንፃር ተቋማዊን ተልዕኮን ሊሸከም የሚችል አደረጃጀትና አሠራር የማሻሻል እንዲሁም ለሥራ ምቹ የሆነ የሥራ አካባቢ መፍጠር፣ ተቋማት የሙስና ስጋት ቅነሣ ስትራቴጂ እንዲያዘጋጁ ዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት ማካሄድ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት፣ የዜጎችን የሥነ-ምግባር እና የሞራል ዕሴቶች ከመገንባት አንፃር እንዲሁም የሙስና መረጃን በመቀበል፣ በማደራጀት በመተንተንና በተገቢው መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ከማድረግ አንፃር አበረታች ውጤት ያስመዘገበ ሲሆን ለ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ መነሻነት ተወስዷል፡፡

በዚሁም መሠረት የ2015 በጀት ዓመት በሀገራችን በአሁኑ ወቅት የሚስተዋለውን ተጨባጭ የሆነ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች ትርጉም ባለው ደረጃ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከላከል የሚያስችል የ2015 የበጀት ዓመት የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ዕቅድ ለመተግበር ተዘጋጅቷል፡፡

ከዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል ሙስና እና ብልሹ አሠራር ሊከላከል የሚችል በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ ዜጋ ለማብዛት ተግባር-ተኮር የሆኑ የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥልጣናዎችን መስጠት፣ ሀብት ለማስመዘገብ በህግ ግዴታ ያለባቸው የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት አመራሮችና ሠራተኞች እንዲሁም የህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ኮሚሽኑ ሥራ ላይ ባዋለው የዲጂታል የሀብት ምዝገባ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ የተዘመገበውን ሀብት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ስራዎችን ማከናወን፣ የተለያዩ የጥቆማ መቀበያ አማራጮችን በማስፋፋትና በማጠናከር ህብረተሰቡ ሙስና እና ብልሹ አሠራሮችን እንዲያጋልጥና እንዲከላከል በየወቅቱ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ማደራጀትና ለሚመለከተው አካላት ተደራሽ ማድረግ ይገኙበታል፡፡

የሥነ-ምግባርና ሞራል እሴት ግንባታ ፕሮግራሞችን በተመለከተ የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ክህሎት የሚመራበት ሥርዓት መዘርጋት፣ ተግባር ተኮር የሆነ የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል አሰልጣኞች አመለካከት ክህሎትና የሥነ-ምግባር አቅምን የሚገነባ ስልጠና መስጠት፣ ከዓለም አቀፍ የፀረ ሙስና አካዳሚ ጋር በመተባበር ለፌዴራል እና ለክልል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችና ከተማ አስተዳደሮች አመራርና ሰራተኞች የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስልጠና መስጠት፣ የ«ፀረ ሙስና» ጋዜጣ ማሳተምና ማሰራጨት ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እንዲሁም በሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ፕሮግራም ስር የሙስና ተጋላጭነትና ሥጋት ጥናት ማካሄድና ምክረ-ሐሳብ ማመንጨት፣ የልማት ፕሮጀክቶች ከሙስና እና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ ተፈፃሚ ስለመሆናቸው መከታተልና ማረጋገጥ፣ የሀገሪቱን የሙስና መከላከልና የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ አፈፃፀም በUNODC ጽ/ቤት ማስገምገም፣ በሚሰጠው ግብረ መልስ መሰረት መርሀ ግብር ማዘጋጀትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣ የፌዴራል፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደር የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግሥት ተሿሚዎች እና አግባብነት ያላቸዉን ባለሙያዎች ሀብትና የገቢ ምንጭ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ምዝገባ እንዲያካሂዱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል መረጃ አስተዳደር መቀበል፣ መተንተንና አስቸኳይ ምክረ ሐሳብ ማቅረብ፣ የሙስና እና ብልሹ አሠራር መረጃ ጥቆማ ቅበላና አስተዳደር ሥርዓት ማዘመንና የሕዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡

በተጨማሪም ተቋማዊ አቅም ማሻሻል እና ብቃት ማረጋገጥ ፕሮግራም ስር የኮሚሽኑን የህግ ማዕቀፍ ዝግጅትና ትግበራ ማሳደግ፣ የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች አመራርና ሰራተኛ የአመራርነትና የሥነምግባር አቅም ማሳደግና ብቃት ማረጋገጥ፣የኮሚሽኑን የሰዉ ኃይል ስምሪት ማጠናቀቅና የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት በቀጣይ 2015 በጀት ዓመት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ይገኙበታል፡፡

በተጨማሪም ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ ከመንግስት የሚመደበውንና ከሌሎች አጋር አካላት የሚኘውን በጀት በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም ረገድ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል፡፡ አጠቃላይ በ2015 በጀት ዓመት ኮሚሽናችን በህግ የተሰጠውን ተልዕኮ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ያቀዳቸው ተግባራት በአመራርና ሠራተኞች ቁርጠኝነት፣ ከክልልና ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ትብብር ተፈፃሚ በማድረግ በሃገር ደረጃ ልማትን ለማረጋገጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ርብርብ የበኩሉን ድርሻ የሚያበረክት ይሆናል፡፡

**ፀረ-ሙስና፤ በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

**አድራሻ**

**ስልክ** 011552-77-79
**ፖ.ሳ.ቁ** 34799
**ኢ-ሜይል** FeaccEthiopia2013@et
**ድረ-ገጽ** www.feacc.gov.et
**ፌስቡክ** www.facebook.com/feaccOfficial
**ቴሌግራም** t.me/feacc
**ትዊተር** www.twitter.com/EthiopiaFeacc
**ዩቲዩብ** Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች** www.feaccdars.gov.et


**ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች**

**ስልክ** 011552-77-92/ 011553-38-52
**ሞባይል** 0935947533
**ፖ.ሳ.ቁ** 34799
**ድረ-ገጽ** www.feacc.gov.et
**ኢ-ሜይል** CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
**ቴሌግራም** t.me/CorruptionPointing
**ዋትስአፕ** wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ቆይታ

# የኮሚሽኑ የ2014 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም እና የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት ጉዳዮች

የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ራሱን በአዲስ መልክ በማደራጀት ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ ከዚህ አንፃር በ2014 በጀት ዓመት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ከመከላከል አንፃር አሰራሩን በማዘመን እንዲሁም ተቋማዊ ብቃቱን ለማሳደግ ሪፎርም አካሂዷል፡፡ ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም እና የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት ጉዳዮችን በተመለከተ ከኮሚሽኑ የየስራ ክፍል ኃላፊዎች ጋር ያደረግነውን ቆይታ ለአንባቢያን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



❖ የተቋም አቅም ብቃትና ማሻሻያን በተመለከተ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጽ/ቤት ኃላፊ ገለፃ ፡-

ኮሚሽኑን ተቋማዊ ለውጥ በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን ያሉ ሲሆን፡-

አንደኛው ህንጻውን በተመለከተ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ኮሚሽኑ ቀደም ሲል ይገለገልበት የነበረው የቢሮ ህንጻ ከግለሰብ በኪራይ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በብዙ መልኩ ተመራጭ አልነበረም፡፡ የኮሚሽኑን ተልዕኮ ሊያሳኩ የሚችሉ የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ሊያግዝ የሚችል በዓመት እስከ 20 ሚሊዮን የመንግስትን በጀት ለህንጻ ኪራይ መክፈሉን በማስቀረት ወጪን ከመቆጠብና ለሌሎች ተቋማት አርዓያ ከመሆን አንጻር ታይቶ እንዲሁም አሰራሮችን በቴክኖሎጂ ታግዞ ለማዘመን በኪራይ የተያዘው ህንጻ አመቺ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ኮሚሽኑ በፊት ሲገለገልበት የነበረውን ካሳንቺዝ የሚገኘውን ህንጻ በበላይ አመራሩ ያላሰለሰ ክትትል በአጭር ጊዜ ውስጥ እድሳት በማድረግ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱንም በማዘመን የስራ አተገባበርን ቀልጣፋ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ሁለተኛው ድግሞ የውስጥ አደረጃጀትን በተመለከተ ሲሆን ኮሚሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የነበረውን አደረጃጀት በመፈተሽ ሙስናን ለመከላከል ያለውን የመንግስትን ቁርጠኝነትና አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ተልዕኮውን ሊሸከም የሚችል አደረጃጀትን በመፍጠር እና ሰራተኞችን በመመደብ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

ከዚህ አንፃር በ2014 በጀት ዓመት የተከናወኑ ተግባራትና የተገኙ ውጤቶች ምን ምን እንደሆኑ ሲያስረዱ፡- በ2014 በጀት ዓመት የተተገበሩ ዋና ዋና ተግባራት በቀደመው ጥያቄ እንደተገለጸው የኮሚሽኑን ተልዕኮ መሸከም የሚያስችል መዋቅራዊ አደረጃጀት የመከለስና የማሻሻል እንዲሁም የኪራይ ወጪን በማስቀረት አሮጌ ህንጻን በማደስና ከኮሚሽኑ ተልዕኮ ጋር የሚጣጣም አደረጃጀትን በመፍጠርና በማዘመን ምቹ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

እንደሀገርም የሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ፖሊሲ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ ህብረተሰቡ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመከታተል ለኮሚሽኑ ጥቆማ እንዲሰጡ አማራጭ ስልቶችን የማዘጋጀትና የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ ከ፲ሺህ በላይ ጥቆማዎች ወደ ኮሚሽኑ ቀርበዋል፡፡ የቀረቡ ጥቆማዎችን በመተንተን ለሚመለከተው ክፍል በማሰራጨት መፍትሄ እንዲያገኙ የማድረግና አስቸኳይ የሙስና መከላከል ማጣራትንም በማድረግ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮችን የማስቆም እና ምክረ-ሀሳብ የመስጠት ስራዎችም ተከናውነዋል፡፡ በሰነድ የነበረ ለህትመት ብዙ በጀትና ቦታንም ይጠይቅ የነበረን የሀብት ምዝገባ አተገባበር ወደ ዲጂታል ተቀይሯል፡፡ አገር አቀፍ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የትስስር ጉባኤ በመመስረት ስራዎችን በጋራ የመገምገምና የማሻሻል ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የሙስና ስጋት ያለባቸውን ዘርፎች በመለየት በሶስት ዘርፎች ላይ ጥናት ተካሂዷል፡፡ ኮሚሽኑ የራሱን የጸረ-ሙስና ጋዜጣም በበጀት ዓመቱ ማሳተም መጀመሩ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

እንደ ወ/ሮ ኮከብ ገለፃ በዚህ ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች በበጀት ዓመቱ ሙስናን በመከላከል ረገድ አዲስ የመንግስትን ምስረታ መሰረት በማድረግ በየተቋማቱ የአደረጃጀት መቀየርና ሪፎርም ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሚደረገው የሙስናን መከላከል ትግል ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው በየተቋማቱ የተመደቡ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት ወጥ አለመሆኑ፣ አንዳንድ ተቋማት ላይ አደረጃጀቱ የተጠናከረ እንዳይሆንና እንዳይኖርም ጭምር የሚደረገው ጥረት እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የየራሳቸውን የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲያቋቁሙ ቢደነገግም አቋቁመው ወደ ስራ መግባት አለመቻቸው ሙስና/ሌብነት ለኢትዮጵያ ስጋት እንዳይሆን እንደ ሀገር በጠበቀ ትስስር ተቀናጅቶ መስራት ላይ ክፍተት የፈጠረ እና እንደ ዋና ተግዳሮት የሚቆጠር ነው፡፡

ኮሚሽኑ ችግሮቹን ለመፍታት ያከናወናቸው ተግባራትስ ምን ይመስላሉ? በሚል ላቀረብንላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ኮሚሽኑ ችግሮቹን ዘለቄታዊ መፍትሄ እስከሚያገኙ ጊዜያዊ መፍትሄ በመስጠት ሲሰራ ቆይቷል። የዩኒቨርስቲ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን በኮሚሽኑ የስራ አደረጃጀት ዘርፎች መሰረት ምደባ በማድረግ ሌሎች የፌደራል ተቋማትን በነበረው አደረጃጀት እንዲቀጥሉ በማድረግ እንዲሁም የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን በመሰብሰብና በማወያየት ጊዜያዊ ተወካዮችን በማስመረጥ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ስራዎች እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡

ካለፉት ተሞክሮዎች በመነሳት በ2015 በጀት ዓመት ኮሚሽኑ ሊሰራ ያቀዳቸው ዋና ዋና ተግባሮችን ያብራሩት ኃላፊዋ

የኮሚሽኑ ራዕይ የሥነምግባር ብቃት በማጎልበት፣ የተቋማት የአሠራር ሥርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ የኢትዮጵያን የሙስና ሥጋት በዘላቂነት ማስወገድ ነዉ፡፡ ይህን ለማሳካት በ2015 በጀት ዓመት በትኩረት ሊተገበሩ የታቀዱ እየተተገበሩም ያሉ የሥነ-ምግባር እና የሞራል እሴቶችን በብቃት መገንባት፣የሙስና ወንጀል እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፣ የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆነ የሕዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣ ህብረተሰቡ የጸረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል፣ በሕግ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና በሕዝባዊ ድርጅቶች ዉስጥ የሚገኙ አመራሮች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ክትትል ማድረግ፣ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ የግልጽነትና የተጠያቂነትን ሥርዓት መፍጠር፣ ከክልሎችና ከሌሎች ተቋማት ጋር ትስስራዊና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ሙስና ለሀገር ስጋት እንዳይሆን ማድረግ ነዉ፡፡



❖ ሙስናን መከላከል፣ ጥናትና ክትትልን በተመለከተ በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት የስራ ክፍል መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ሙሉጌታ ገለፃ፡-

በፀረ-ሙስና ትግልና ስትራቴጂ ዉስጥ ‹‹የሰዶ ማሳደዱን›› ዉጣ ዉረድ በእጅጉ ከመቀነስ አኳያ የመከላከሉ ስራ እጅግ ተመራጩ መንገድ መሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህም በመነሳት የሙስና መከላከል ጥናት የሥራ ክፍል በዋናነት የወንጀሉን ባህሪ በሚመጥን መልኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የተቋማት አሰራር በመዘርጋት ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተልዕኮን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ተደራጅቶ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

እንደ አቶ አክሊሉ ገለፃ በ2014 በጀት አመት ዘርፍ-ተኮርና መዋቅራዊ የሙስና ሥጋቶችን ለይቶ መከላከል አስፈላጊ አቅጣጫ መሆኑን በመገምገም በኢኮኖሚ ዘርፍ በገቢዎችና ጉምሩክ፣ በማህበራዊ ዘርፍ በትምህርት እና በአስተዳደር ዘርፍ ደግሞ ፍርድ ቤቶችን ከፌዴራል እስከ ክልል በተዘረጉ መዋቅሮች የሙስና ሥጋት ጥናት በማካሄድና ሪፖርት በማዘጋጀት የመጀመሪያ ዙር የባለድርሻ አካላት ውይይት ማድረግ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት የፌደራልና የክልል

## ቆይታ

የፀረ-ሙስና ተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ክፍተት ሊፈጥሩ የሚችሉ 62 አሠራሮችን እንዲሁም የፌደራል ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ደግሞ 248 አሠራሮችን በድምሩ 310 የአሠራር ክፍተቶችን በመለየት የሙስና መከላከል የአሰራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሚመለከታቸዉ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡ ጥናቶቹ የመንግስት ፕሮጀክትና ግዥ አፈፃፀም፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች የፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ኮሚሽኑ ለ2015 በጀት ዓመት በተለየ ሁኔታ በተመረጡ የትኩረት መስኮች ዘርፍ-ተኮርና የተቀናጀ የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ለማድረግ እንዳቀደ ጠቁመው ዕቅዱ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ሥጋት በሆኑ እና በተለዩ የትኩረት መስኮች ላይ የተቀናጀ አገራዊ የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል በማድረግ ምክረ-ሐሳብ በማመንጨት ጥራትና ተገቢነት ያላቸዉ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት አጠቃላይ አላማ ያለዉ ነው፡፡ የተቀናጀና ዘርፍ-ተኮር የሙስና እና የብልሹ አሠራር መከላከል ጥናትና ክትትል በፌደራል መንግስት ተቋማት፣ በልማት ድርጅቶችና በሕዝባዊ ተቋማት ላይ መሰረት ባደረገ መልኩ ይተገበራል፡፡ በዚህም የመንግሥት አካላት (አስፈጻሚ፣ ሕግ አዉጪ እና ሕግ ተርጓሚ) እና በሥራቸዉ በየአስተዳደር ወሰን የሚገኙ ተቋማት እንደዘርፍ በመዉሰድ በተመረጡ ርዕሰ-ጉዳዮች አገራዊ ይዘት ያለዉ ጥናትና ክትትል ከክልል/ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች ጋር በመቀናጀት ይከናወናል፡፡

እቅዱ በዋናነት በተለዩ የትኩረት ዘርፎች/አቅጣጫዎች ላይ ተመስርቶ የሚተገበር ሲሆን እነዚህም የከተማ መሬት አስተዳደር እና ሙስና፣ የመንግስት ተቋማት ከፍተኛ ግዥዎችና የአቅርቦት ሰንሰለት እና ሙስና፣ የፋይናስ ተቋማት የብድር አቅርቦት/የዉጭ ምንዛሪ አስተዳደር እና ሙስና፣ የከተማ ቤቶች ልማት/አስተዳደር እና ሙስና፣ የገቢዎች እና የጉምሩክ አስተዳደር አሠራር እና ሙስና፣ የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሠጣጥ ግልጽነት እና ሙስና፣ የመንግሥት ተቋማት የፕሮጀክት አስተዳደር እና ሙስና ያካተተ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም አቶ አክሊሉ እንደተናገሩት ለዕቅዱ ዉጤታማነት ከዘርፉ ባለሙያዎች ባሻገር በተለይም የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤት የሆኑ የመንግስት ተቋማትና ማህበራት እንዲሁም ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ለጉዳዩ ተገቢዉን ትኩረት ሰጥተዉ ከኮሚሽኑ ጋር በመቀናጀት የሚጠበቅባቸዉን ድርሻ እንዲወጡ ጠቁመዋል፡፡



❖ በሥነ-ምግባርና ሞራል እሴቶች ግንባታ ዙሪያ በኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና የባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ የስራ ክፍል መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ አዲስ ለማ ገለፃ፡-

ከፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎች መካከል አንዱ የዜጎችን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች በብቃት በመገንባት የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋር እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ ኮሚሽኑ ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል የአሠራርና የአደረጃጀት ማሻሻያ በማድረግ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ በዚህ መሠረት ኮሚሽኑ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በፅናት የሚታገል ትውልድና ማህበረሰብ በዘላቂነት ለመገንባት የክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በ2014 በጀት ዓመት በሥነምግባርና ሞራል እሴቶች ግንባታ ዙሪያ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሥልጠናና የግንዛቤ ማኅልበቻ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

አቶ አዲስ ሲያብራሩ በበጀት አመቱ በመንግስት ተቋማት፣ በመንግስት የልማትና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ ከመሆን አንፃር በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኙ ተቋማትን በመለየት ለአመራሮቻቸው፣ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውና ለሠራተኞቻቸው ግንዛቤ ማስጨበጫና ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም በፌደራል ተቋማት ለሚሰሩ 5000 አመራሮች እና ሰራተኞች በተመረጡ የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ከዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና አካዳሚ (IACA) ጋር በመተባበር ለ50 የፌደራል እና የክልል ኮሚሽን አመራሮች እና ሰራተኞች በሙስና ስጋት ጥናት፣ በጥቅም ግጭት እና አመራር ሥነምግባር ላይ የዓቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር በክልሎች የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አማካኝነት በዞንና በወረዳ ለሚገኙ 1 ሚሊዮን 333 ሺህ 629 ለሚሆኑ የመንግስት ሰራተኞች፣ አመራሮች እና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሥነ-ምግባር፣ በሞራል እሴቶች ግንባታና በሙስና መከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከመድረክ ባሻገር የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች በብሮድካስት፣ በማህበራዊና በህትመት ሚዲያ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት ከባለፈው በጀት ዓመት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ የታዩ ድክመቶችን በማረምና በሥነምግባር ዘርፍ ትኩረት በሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በማተኮር በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን ታቅዷል፡፡

በዚህ መሠረት በበጀት ዓመቱ የሙስና ስጋት ጥናት በሚካሄድባቸዉና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ በሆኑት በከተማ መሬት አስተዳደር፣ በመንግስት ትላልቅ ግዥዎች፣ በፋይናንስ ተቋማት፣ በከተማ ቤቶች ልማት፣ በገቢዎችና ጉምሩክ እንዲሁም በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስር ለሚገኙ 1150 ሠራተኞቸና አመራሮች፣ ለ2,815 የፌደራልና የክልል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎችና ሠራተኞች፣ ለ115 የፌደራልና የክልል የሥልጠና ባለሙያዎች ሥልጠና ይሰጣል፡፡ 300 ለሚሆኑ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ደግሞ በሥነ-ምግባር እና የሞራል እሴቶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ 10 የምክክር፣ የፓናልና የግንዛቤ ማኅልበቻ መድረኮችን በማዘጋጀት በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንደሚደረግ አቶ አዲስ ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም እንደ አቶ አዲስ ገለፃ በሥነ-ምግባር ዘርፍ ስር የሚከናወነው ተግባር በየተቋማቱ የሚገኙ ትናንሽ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችን ማደራጀት፣ ማብቃት መከታተልና መደገፍ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በፌደራልና በክልል ለሚገኙ 7,828 ለሚሆኑ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሀገራዊ ዘርፍ ተኮር እንቅስቃሴ የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ተቋማት እና ግለሰቦች እውቅና ወይም ሽልማት (Integrity Excellence Award) እንዲሰጣቸው የሚደረግ ሲሆን ዓመታዊ የሙስና መከላከል የግልፅነት ደረጃ (Annual Institutional Transparency Index ) በማውጣትም ለህዝብ ግልፅ የማድረግ ተግባር ይከናወናል፡፡



❖ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት ማስወገድ ስራ ክፍል መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን በላይነህ ገለፃ፡-

በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2002 ዓ/ም እና የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት ልማት እና የህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ተመራጮች፣ ተሿሚዎች፣ የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያሳውቁ እና እንዲያስመዘግቡ የህግ ግዴታ ይጥላል፡፡

የሀብት ምዝገባ መረጃን በመተንተን እና በማረጋገጥ የጥቅም ግጭትን በመለየት እና በመከላከል በመንግስት ተቋማትና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና ስጋት መቀነስ እና ማስወገድ ከስራ ሂደቱ የሚጠበቁ ዋና ዋና ተግባራት ሲሆኑ በ2014 ዓ.ም ይህን ተግባሩን ሲያከናወን መቆየቱን አቶ መስፍን ጠቁመዋል፡፡ በዋናነት ላለፉት 9 ዓመታት የተጓተተው የዲጂታል የሀብት ምዝገባ ፕሮጀክት ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ተገምግሞ( Disclosure Asset Registration System-DARS) ሶፍትዌርን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጥታ የሀብት ምዝገባ (Online Registration) ተግባር የተከናወነበት ዓመት እንደነበር አቶ መስፍን አስታውሰው በዚህም ለሀብት ምዝገባ ቅፅ በየዓመቱ የሚፈፀምን የህትመት ግዥ ከፍተኛ ወጪን እና ሰነድ ማከማቻ ተጨማሪ ቦታ/ቢሮ ዝግጅትን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ተችሏል፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለፃ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥቅም ግጭት ማስተዳደርና መከላከል ሥርዓት ስልጠና እንዲሰጥ እና የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ተግባር ጅማሮ በቂ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ የሀብት ምዝገባ መረጃ ስርዓትን በመንግስት ተቋማት ከመተግበር አኳያ ለ2,547 የሥነ-ምግባር መከታተያ ኃላፊዎና ባለሙያዎች በDisclosure and asset registration system ላይ ቴክኒካል ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ጤና ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር እና የልማት ድርጅት አመራሮች ሀብትና የገቢ ምንጫቸውን በቀዳሚነት የቀጥታ የሀብት ምዝገባ /Online Registration እንዲያካሄዱ ተደርጓል፡፡ ሌላው በበጀት ዓመቱ በ247 ሀብት አስመዝጋቢዎች ላይ የሀብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማጣራት ተሰርቷል፡፡

የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት ማስወገድ የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት ጉዳዮችን በተመለከተ የገለፁት ስራ አስፈፃሚው የሀብት ምዝገባ የመረጃ ስርዓት (Disclosure and asset registration system) ከመዘርጋቱ በፊት የተካሄደ የሰነድ ሀብት ምዝገባ መረጃዎችን ዲጂታላይዜሽ ሥራ ማከናወን፣ የሀብት ምዝገባ የመረጃ ስርዓት በፌደራል ተቋማት፣ ህዝባዊ ድርጅቶች እና በክልሎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የተመዘገበ መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ ማከናወን እና የጥቅም ግጭት ማስወገድ ተግባራትን ማከናወን የስራ ክፍሉ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎቹ ናቸው፡፡



# ሳይቃጠል በቅጠል

# የጥቅም ግጭትና ውሳኔ አሰጣጥ



ለአንድ ሀገር ዕድገትና ልማት የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እና የሰው ሀይል ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ ነገር ግን ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ዜጎችን ወደ ተሻለ ደረጃ ከመለወጥ ባሻገር የሀገርን በጎ ገጽታ መለወጥና አለምአቀፍ ተፅኖ መፍጠር ይቻላል፡፡

ከህዝብና መንግስት በአደራ የተሰጠን ኃላፊነት ለግል ጥቅምና ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ የህዝብን ጥቅም ወደ ጎን አድርጎ መስራት ሀገርን ለከፋ ድህነትና ኃላቀርነት ከመዳረጉም ባለፈ ውሎ አድሮ የወንጀል ተጠያቂ ሊያደርግ እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ህዝብ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት መሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግሰት አንቀፅ 8 እንዲሁም የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ መሆኑን በአንቀፅ 40(3) በግልፅ ያመላክታል፡፡ በዚሁ አግባብ በኃላፊነት በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሆነው በህዝብ ሀብት ላይ ውሳኔ የሚያሳልፉ ውሳኔ ሰጪዎች በአደራ ወይም በውክልና የተሰጣቸውን ስልጣን በግልፅ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ ሌላው ከህዝብና መንግስት የተሰጠን ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣት ለመከላከል እንዲያስችል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግሰት አንቀፅ 12(1) ላይ የመንግስት አሠራር በግልፅነትና ተጠያቂነት ላይ ተመስርቶ መከናወን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

በዚህ ጹሁፍ የጥቅም ግጭትና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ከትርጉም ጀምሮ ሊያስከትል ስለሚችለው የተጠያቂነት ጉዳይ ለአንባቢያን በአጭሩ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

የጥቅም ግጭት ምንድን ነው? እንዴት ሊከሰት ይችላል? በምን ሁኔታ ይከሰታል? ለሙስና መከሰት መነሻ ሊሆን ይችላል? ከውሳኔ አሰጣጥ ጋር በምን ይያያዛል? የጥቅም ግጭትን እንዴት መከላከል ይቻላል? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስቶ ለአንባቢያን በተቻለ መጠን ግልጽ ማድረግ ጠቃሚና አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት እንደየ ሁኔታው የተለያየ ትረጉም ያለው ቃላት ቢሆንም ለእዚህ ጻሁፍ በአጭሩ ለማሰቀመጥ አንድ የሥራ መሪ፣ ባለስልጣን፣ የመንግስት ሰራተኛ፣ የህዝብ ድርሻ ያለበት ሽርክና ማህበር ወይም ድርጅት የሚሰራ ሰው ከህዝብና ከድርጀቱ ህጋዊ ጥቅም በተቃረኒ መልኩ በራሱ ፍላጎት ተመስርቶ፤ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ወይም በገንዘብ ጥቅም በመደለል ወይም በመማለል ወይም በቤተሰብና በቡድን አስተሳሰብና ፍላጎት ተፅዕኖ ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ተፅዕኖ ስር በመውደቅ በህዝብና መንግስት የተሰጠውን የስራ ድርሻ ህግን መሰረት አድርጎ መሰራት የሚገባውን ጉዳይ ወደ ጎን በማድረግ ውሳኔ የወሰነ፣ ለወደፊት ለሚገኝ ጥቅም የማለለ እና የጥቅም ተገኘነት ሁኔታ ተገማች ድርጊት የፈጸመ ሲሆን የጥቅም ግጭት ተፈጥሯል ማለት ነው፡፡

የጥቅም ግጭት በማንኛውም ተቋም፣ ድርጅት፣ የስራ ኃላፊነት፣ ውሳኔ ሰጭነት ደረጃ ሊከሰት የሚችል ነገር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ውሳኔ ሰጭነትና ጥቅም ግጭት የሚከሰተው በባለስልጣን ደረጃ ብቻ የሚፈጸም ድርጊት የሚመስለው በርካታ የማህበረሰብ ክፍል አንደሚኖር መገመት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የጥቅም ግጭት በማንኛውም ደረጃ ባለ ግለሰብ የሚፈጸም እና እየተፈጸመ ያለ ክስተት መሆኑን በርካታ መረጃዎችና ማሳያዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በአንድ ተቋም ከአለው የስራ መሪ ወይም ባለስልጣን ጀምሮ አስከ ጥበቃ፣ ንብረት ክፍል፣ ሾፌር፣ ተላላኪ ወይም ቢሮ ረዳት አንዲሁም የጽዳት ሰራተኛ ድረስ በየደረጃው ለጥቅም ግጭት የሚጋለጡበት ሁኔታ ወይም ዕድል ሰፊ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ብለን ስንነሳ ከምንም ነገር የሚነሳ አይደለም፣ የጥቅም ግጭት እና የሙስና ትርጉም አንድነትና ልዩነታቸዉን በግልፅ የሚያብራራ ማስረጃ ባይገኝም ለሙስና መከሰት ወይም ሙስና የተከሰተበት ቦታ ሁሉ የጥቅም ግጭት መኖሩን መረዳት ይቻላል፣ የጥቅም ግጭት በተፈጠረበት ሁኔታ ዉስጥ ሁሉ የሙስና ተግባር አይከሰትም ይሁን እንጂ ሙስና በተከሰተበት ሁኔታ የጥቅም ግጭት የመከሰት እድል ይኖረዋል፡፡ ይህ የሚያመላክተዉ የጥቅም ግጭት ሙስና እንዲከሰት መልካም አጋጣሚዎችን ወይም ለሙስና መከሰት ምቹ መንገድን የሚፈጥር ሲሆን፣ የጥቅም ግጭት በራሱ ሙስና አለመሆኑ እና የተፈጠረዉ ምቹ ሁኔታ በተግባር ከተደገፈ ሙስና ተከስቶ እናገኘዋለን፡፡ በአጭሩ የጥቅም ግጭት ለሙስና መከሰት መንገድ ጠራጊ ነዉ፡፡

ጥቅም ግጭት በአብዛኛው ከሰራተኛ ቅጥር ዕድገትና ዝውውር፣ ከግዥ ሂደት በተለይ ከትላልቅ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግዥዎች ጋር፣ ሙያዊ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር፣ ከተለያዩ አገልግሎትና ፈቃድ ሰጭ አካላት ጋር፣ ህግና ደንብ አንዲሁም መመሪያ ሲዘጋጅ ለተወሰና አካል ጥቅም አንዲሰጥ ከማድረግ አንጻር፣ ከዕርዳታ ስርጭትና ክፍፍል፣ ከብድርና ኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ ከጉሙሩክና ገቢ መሰብሰብ ሂደት ጋር በተያያዘ፣ ከመምህራንና ህክምና ባለሙያች ጋር ወዘተ…አያይዞ መመልከት ይቻላል፡፡ የጥቅም ግጭት በተቋማት የውሳኔ ሰጭነት ደረጃ የሚከሰት ክስተት ከሆነ በምሳሌ እንዴት ማስረዳት ይቻላል? ከምን ከምን ጋርስ ሊያያዝ ይችላል? የሚሉትን ነጥቦችን በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## የጥቅም ግጭት ከትምህርት ጋር

አንድ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምር መምህር ወይም ሌክቸረር በሚከፈለው ደመወዝና የሙያ ሥነ-ምግባር በሚፈቅደው መሰረት የተሰጠውን የተማሪዎች ክፍለ ጊዜ በታታሪነትና በሀገር ፍቅር ስሜት በሚገባ ለተማሪዎቹ እውቀትና ክህሎት ማዋል ሲገባው የራሱን የግል ፍላጎት ለማርካት ሲል ለሌላ ገንዘብ ለሚያስገኝለት የግል ትምህርት ቤት ካዋለው እና በመንግስት ትምህርት ቤት የተማሪዎች ክፍለ ጊዜ

## ሳይቃጠል በቅጠል

የሚቃጠል ከሆነ እንዲሁም ለይስሙላ ተማሪዎች ማግኘት የማይገባቸውን ውጤት እየሰጡ ወደ ቀጣዩ ክፍል ማሳለፍ ብሎም ማስመረቅ ተማሪዎቹን ከመጉዳት ባለፈ በጥቅል ውጤቱ ሀገርን ይጎዳል፡፡

ይህም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያለፈ ተማሪ ነገ የሀገር ተረካቢ ሆኖ በተለያየ ስራ መስክና ኃላፊነት ሊሰማራ ይችላል እንዲሁም ድርጊቱ የተከበረውን ሙያ ያለምንም ድካምና ምዘና በገንዘብ እንደመሸጥ ይቆጠራል ብሎም በገንዘብ የማይተመን ተደራራቢ እና ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር አሉታዊ ችግር የሚፈጥር ማህበራዊ ጠንቅ ይሆናል፡፡

ሌላው ማሳያ የግል ትምህርት ተቋማት አስፈላጊውን መሰፈርት ሳያሟሉ ፈቃድ በሚሰጠው አካል በተለይ በከፍተኛ ትምህርትና አግባብነት ባለስልጣን የሚፈቀድ ከሆነ ችግሩ እየተባባሰ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ከመዋለ ህጻናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት በዚሁ ችግር ተተብትበው እንደሚገኙ የዕየየለቱ ዜና ሆኗል፡፡



### የጥቅም ግጭት በህክምና አገልግሎት ዘርፍ፣ በግዥና ሰው ኃይል ቅጥር

አንድ የህክምና ዶክተር በመንግስት ሆስፒታል እየሰራ ደንብና መመሪያ በማይፈቅደለት መልኩ ለራሱ ጥቅም ሲባል በመንግሰትና ህዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት ወደ ጎን ትቶ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ይህም የጥቅም ግጭት ማሳያ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሰራተኛ ቅጥር እና እድገት የሚሰሩ ኃላፊነት የተጣለባቸው ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች ህጉ በሚፈቅደው ሁኔታ ጥራትና ውድድርን መሰረት አድርገው ለተቋማቸው ጥቅም ቅጥር መፈጸም ሲገባቸው ጥቅም ለማግኘት ሲባል በዘመድ አዝማድ፣ በቡድን ጥቅም፣ በዘር ፣ በመጥፎ ግንኙነት ተመስርተው ስራቸውን ካከናወኑ ይህም የጥቅም ግጭት ብሎም ሙስና ነው ማለት ነው፡፡

በተመሳሳይ አንድ የግዥ ኃላፊ ወይም ባለሙያ የመንግስት ግዥ ህግና መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ ደረጃውን ያላሟላ ወይም የህዝብና ሀገር ጥቅም በሚጎዳ ሁኔታ ለራስ ጥቅም ወይም ሌላ ሰው ወይም ድርጅት ጥቅም ለማስገኘት ከጨረታ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ግዥ ማጠናቀቂያና ርክክብ ሂደት ውሳኔን በማዛባት፣ መረጃ በመስጠት ወይም በሌላ ሁኔታ ጎጅ ውሳኔዎችን ማሳለፍ አንዱ የጥቅም ግጭት መገለጫ ብሎም የሙስና ወንጀል ድርጊት ማሳያ ነው ማለት ነው፡፡

### ዳኛና የጥቅም ግጭት

ዳኞች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ገለልተኛና ያለአድሎ ሊሆን እንደሚገባ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ተደንግጓል፡፡ የጥቅም ግጭት የዳኝነት ገለልተኝነትን ከሚያሳጡ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ዳኞች ከተከራካሪ ወገኖች እና ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር ካላቸው ግንኙነት አንፃር እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አያሰኝም የሚያስብል ሁኔታዎች ሲኖር የጥቅም ግጭት ሊከሰት እንደሚችል፣ ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት የጥቅም ግጭት የሚፈጠረው ዳኛው ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ ነው፡፡

ዳኛው ከተከራካሪዎቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረፈጅ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር የሆነ እንደሆነ የጥቅም ግጭት ሊያስከትል ይችላል፡፡ አንድ ዳኛ በዳኝነት ከመሾሙ በፊት በጥብቅና ሙያ ተሰማርቶ እያለ ለደንበኛው የጥብቅና አገልግሎት የሰጠበት ጉዳይ በዳኝነት ከተሾመ በኋላ ዳኝነት እንዲሰጥበት ቢቀርብለት የጥቅም ግጭት እንደተከሰተ ይቆጠራል፡፡ በተጨማሪም ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ የጥቅም ግጭት እንደተከሰተ ይቆጠራል፡፡

### ዐቃቤ ህግና የጥቅም ግጭት

ዓቃቤ ህግ የሕዝብን እና የመንግስትን ጥቅም በማስከበር ረገድ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩም ሆነ በፍታብሔር አስተዳሩ ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡ የወንጀል ምርመራን በመምራት፣ ክስ በመመስረት፣ በመከራከር እና የፍርድ ቤት ትዕዛዛት አፈፃፀማቸውን በመከታተል እንዲሁም የመንግስት ጥቅም ባለባቸው በፍታብሔር ጉዳዮች መንግስትን በመወከል ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም የዳኝነት ሰሚ አካል ክስ ይመሰረታል፣ ይከራከራል ወይም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ጣልቃ ገብቶ ይከራከራል፡፡

ዓቃቢ ህግ በሕግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በመፈፀም የሕዝብ ጥቅምን ሲያስከብር በሕግ የተመለከቱ አሰራሮችን፣ ሥነ-ስርዓቶችን እና የሙያ ሥነ-ምግባር መርሆዎችን በመከተል መሆን ይገባዋል፡፡ ዐቃቤ ህግ የሚፈጽማቸውን ተግባሮች በጠቅላላው የመላው ህዝብ ጥቅም የሚመለከቱ መሆናቸውን ምን ጊዜም መዘንጋት የለበትም፡፡ ሆኖም ግን ዓቃቤ ህግ የሕዝብ ጥቅምን ለማስከበር የያዘው ጉዳይ ከግል ጥቅሙ ጋር የሚጋጭበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፤ የዘመዶቹ ወይም የቅርብ ወዳጆች የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከስራው ወይም በስራው ምክንያት ከያዘው የህዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ችግር ለበላይ ኃላፊው ወዲያውኑ በማሳወቅ ጉዳዩ በሌላ ዐቃቤ ህግ እንዲታይ ማመልከት አለበት፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

### ጠበቃና ጥቅም ግጭት

ማንኛውም ጠበቃ በራሱና በደንበኛው ወይም በዘመዶቹና በደንበኛው ወይም በሸሪኮቹና በደንበኛው ወይም በሁለት ደንበኞች መካከል የጥቅም ግጭት መኖሩን እያወቀ የሙያ አገልግሎት መስጠት አይችልም፡ ፡ የጥቅም ግጭት መኖሩ የታወቀው አገልግሎቱ ከተጀመረ በኃላ ከሆነ ይህንኑ ለደንበኛው አስረድቶ አገልግሎቱን ማቋረጥ አለበት፡፡

በተለይም ጠበቃው በአንድ በኩል ከደንበኞቹ ለአንደኛው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጥቅም ወይም ባለቤት መሆን ይገባዋል የሚልበትን ህጋዊ ክርክርና ማስረጃ በማቅረብ የዚሁኑ ደንበኛ መብት ለማስከበር እየተሟገተ በሌላ በኩል በተመሳሳይ ሁኔታ የመብት ተጠቃሚው ሌላኛው ደንበኛ ነው ብሎ ለማሳመን መሞከር አይችልም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ጠበቃው ለደንበኛው ታማኝ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ የጥቅም ግጭት በተለያየ ደረጃና የውሳኔ ሂደት የሚከሰት ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት ከመሆኑም በላይ ድርጊቱ ተፈጽሞ ሲገኝ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የሙስና ወንጅል ድርጊት ሆኖ በወንጀል የሚያስጠይቅ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው፡፡

### ለጥቅም ግጭት የሚገፉፉ ወይም የሚያጋልጡ ምክንያቶች

- ተቋማት የጥቅም ግጭትን የሚከላከል መመሪያ አለመኖር እና የጥቅም ግጭትን አይቶ እንዳለዩ ማለፍ ወይም መታገስ ወይም እርምጃ አለመውሰድ ፣
- ተከስቶ ሲገኝም ደካማ አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ቅጣት መጣል፣
- ደካማ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መኖር፣
- የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት አሰቀድሞ አለማሳወቅ ወይም አለማንቃት፣
- የሥነ-ምግባር መመሪያ ወይም ደንብ አለማዘጋጀት/ አለመኖር፣
- የግልጽነትና ተጠያቂነት ሥርዓት አለመዘርጋት/አለመኖር፣
- የግለሰቡ ስብዕና/ሥነ-ምግባር መጓደል፣
- የግንዛቤ እጥረት/ ጉዳዩ እንደሚያስጠይቅ አለማወቅ፣
- በመንግስት ግዥ መመሪያ ላይ ደካማ ግንዛቤ መኖር፣
- የተሰጠውን ስራ በኃላፊነት እና ተጠያቂነት መንፈስ አለማከናወን እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### የጥቅም ግጭት እንዴት መከላከል ይቻላል?

- የጥቅም ግጭት መመሪያ ወይም ደንብ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ ለሰራተኞችና ኃላፊዎች በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ መቻል ይኖርበታል፣
- የጥቅም ግጭት የሚከሰትባቸው ቦታዎችን ወይም የስራ አካባቢዎች መለየትና ደረጃ በመስጠት መከላከያ መፍትሄ ማዘጋጀት፣
- ውሳኔ የሚሰጠው አካል ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው አካል የሚሰጠው ውሳኔ ትክክለኛና ግልጽ ነው ብሎ ደጋግሞ ማሰብና ሁኔታውን ማወቅና የጥቅም ግጭት ካለው ከድርጊቱ መቆጠብ፣
- ይህን ውሳኔ የምወስነው በትክክል ከጥቅም መነሻ እና ፍላጎት ውጭ ነው ወይስ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ በሚል መመዘንና ተገቢ ካልሆነ መተው፣
- አገልግሎቱን የሚፈልገው አካል ወይም ድርጅት ተጽዕኖ አሳርፎብኛል?፣
- የተሰጠው ውሳኔ ተቋሙን ወይም መንግስትን ይጎዳል ወይ?፣
- የሀብት ምዝገባና ማሰወቅ አዋጅን ተግባራዊ ማደረግ፣ ትንተና በመስራት፣ ማጣራትና በማረጋገጥ ከሚገመተው በላይ ሀብት ይዞ የተገኘን በመንግስት ተቋም፣ በሽርክና ማህበር፣ በህዝባዊ ድርጅቶች እና የህዝብ ጥቅም ባለባቸው ሁሉ የሚሰራን ግለሰብ/ሰው በህግ ተጠያቂ ማድረግና የማስረዳት ሸክሙን እንዲወጣ በማድረግ በፍርድ ቤት ከተገቢ በላይ ሆኖ ከተገኘ እንዲወረስ ማድረግ፡፡
- አንዳንድ ስጦታዎች ምንም እንኳን ከመልካም ዓርአያነትና ከትክክለኛ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ሊሆኑ ቢችሉም ከስጦታ ጋር ተያይዞ ውሳኔን ሊያዘባና ከጥቅም ግጭት ሊያያዙ ስለሚችሉ ስጦታን በተመለከተ ተገቢውን ተቋማዊ መመሪያ አስቅድሞ በማዘጋጀት መተግበር፡፡ ስጦታ የተበረከተለት ግለሰብ፣ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ለተቋሙ ይፋ እንዲያደርግ ማስገደድ፡፡

በተጨማሪም እንደ ጊዜውና ሁኔታው ተገቢውን መመሪያ በማዘጋጀት ጥቅም ግጭትን መከላከል በቅድሚያ የተቋም ኃላፊዎችና በውሳኔ ሰጭነት የተቀመጠው ሰው መሆኑን ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ማስገንዘብ ይገባል፡፡

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

# የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች

የሥነ-ምግባር ህግጋትን ጥሶ ያልሰራበትን ለማጋበስ የሚቋምጠውን፣ ያልተፈቀደለትን ለመሰብሰብ የሚሯሯጠውን፣ አደራ ለመብላት የሚያደባውን፣ ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የተሳነውን አደብ ለማስገዛት አንድም ማለፊያ መምህር እንቢ ላለው ደግሞ ሁነኛ መቅጫ መሳሪያ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል መልካም ሥነ-ምግባርን ለማስፈን እና ሙስናን የማይሸከም ትውልድ ለማፍራት ትምህርቱን ለማዳረስ የፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥረት እያደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህገ-ወጦችን ለፍርድ በማቅረብ የሙስና ወንጀል በሃገር እና በዜጎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የፍትህ አካላት የህግ ማስከበሩን ሥራ ጠንክረው በመሥራት ላይ ናቸው፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነ-ምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ትምህርት ባለፉት ዓመታት በስፋት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ኮሚሽኑ በ2014 ዓ.ም ሠፋፊ የሪፎርም ሥራዎችን ማለትም ተቋማዊ አቅም እና ብቃት ከማረጋገጥ አንፃር ተቋማዊ ተልዕኮን ሊሸከም የሚችል አደረጃጀትና አሠራር የማሻሻል እንዲሁም ለሥራ ምቹ የሆነ የሥራ አካባቢ መፍጠር፣ ተቋማት የሙስና ስጋት ቅነሣ ስትራቴጂ እንዲያዘጋጁ ዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት ማካሄድ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት፣ የዜጐችን የሥነ-ምግባር እና የሞራል ዕሴቶች ከመገንባት አንፃር እንዲሁም የሙስና መረጃን በመቀበል፣ በማደራጀት በመተንተንና በተገቢው መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ከማድረግ አንፃር አበረታች ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በሕግ ማስከበር ረገድም ኃላፊነቱ የተሰጣቸው የፍትህ አካላት ከመዝባሪዎች እና አደራ በሎች ጋር እየታገሉ የሀገርን ኃብት ከጥፋት ለመታደግ ይተጋሉ፡፡ መንግስትም የሕግ ማስከበሩ ሥራ ሕጋዊ መሰረት ለማስያዝ ይቻል ዘንድ የሙስና ወንጀል ናቸው ተብለው በህግ የተዘረዘሩት ጥሰቶች እና የሚያስከትሉት ቅጣት በተለያዩ ጊዜያት የሃገሪቱ ሕግ ሆነው ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ኃላፊነቱን ተወጥቷል፡፡ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ ውስጥ የሙስና ወንጀሎችም መካተታቸው መንግስት ሙስናን አምርሮ ለመታገል ያለውን ቁርጠኝነት አመላካች ነው፡፡ በዚህ ሕግ ውስጥ በአፈጻጸም ወቅት የታዩ ግልጽነት የሚጎድላቸውን ድንጋጌዎች ግልጽ ማድረግ እና ማሻሻል በማስፈለጉ በ2007 ዓ.ም የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ህግ ሆኖ ጸድቋል፡፡ በዚህ አዋጅ ውስጥ ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝብ የተሰበሰበ ሀብት በሚያስተዳድሩ በግል ዘርፉ አካላት የሚፈጸሙ ተመሳሳይ ወንጀሎችም እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሃገራችን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ ሕብረት የሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን ፈራሚ ሃገር በመሆኗ በእነዚህ ኮንቬንሽኖች መሰረት ደግሞ በግል ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚፈጸሙ የጉቦኝነት እና የምዝበራ ተግባራት በሙስና ወንጀልነት እንዲካተቱ ስለሚያስገድዱ ሕጉን ከዚህ አኳያ ማሻሻል አስፈልጓል፡፡ በዚህ መሠረት በአዋጁ የሙስና ወንጀሎች ናቸው ተብለው የተጠቀሱ ድርጊቶችን በዚህ ጽሁፍ በአጭር በአጭሩ ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡








## 1.በስልጣን አላግባብ መጠቀም

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት አሊያም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ የተሠጠውን ሹመት፣ ስልጣን፣ ኃላፊነት በግልጽ በተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ ሲገለገል በስልጣኑ አላግባብ ተጠቀመ ይባላል፡፡ እንዲሁም ከተሠጠው ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ ወይም ከስልጣኑ ወይም ከኃላፊነቱ ከተሻረ፣ ከተዛወረ፣ ከታገደ በኋላ የሠራበትም እንደሆን ስልጣኑን ያለግባብ እንደተጠቀመ ይቆጠራል፡፡



## 2. ጉቦ መቀበል

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነት ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለራሱም ይሁን ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡



## 3. የማይገባ ጥቅም መቀበል

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ወይም ከፈጸመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆን በሙስና ወንጀል ተከሶ በህጉ መሠረት ቅጣት ይጣልበታል፡፡

## 4. አስታራቂ ሽማግሌዎች እና ሌሎች ሰዎች የሚፈጽሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል

ማንኛውም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ ወይም አጣሪ፣ ሥራውን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን ማንኛውም ልዩ አዋቂ ወይም ኤክስፐርት እንዲሁም ገቢና ወጪ ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር ወይም ግንባታ በተገባ ውል መከናወኑን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተው ሰው ላይ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም የተቀበለ ሙሰኛ ተብሎ ዘብጥያ እንደሚወርድ በህጉ ተመላክቷል፡፡

## 5. የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅትን ሥራ በማያመች አኳኋን መምራት

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ስልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የንግድ ወይም የሌላ ሥራ ውል ከተዋዋለ ሥልጣን የሰጠውን አካል ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸውም ዘዴ የፈጸመ እንደሆን ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት የሚለው አንቀጽ ተጠቅሶበት ፍርድ ቤት ይቆማል፡፡

## 6. አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በህግ አግባብ ሳይፈቀድለት እና የግል ንብረቱ ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበውን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ ባለዋጋ ነገር ወይም አደራ እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ የከፈተ ያስከፈተ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆን አለበለዚያም ለራሱ የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የሰጠ እንደሆነ እና ይህም በመረጃ ከተረጋገጠ እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ እስር ይጠብቀዋል ወይም እስከ ሰባት ሺኅ ብር ይቀጣል፡፡

## 7. በሥራ ተግባር የሚፈጸም የመውሰድና የመሠወር ተግባር

የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠቀምባቸውን ዕቃዎች ሰነዶች ባለዋጋ ነገሮች ጥሬ ገንዘቦች አላቂና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ ሙስና ከፈጸሙ ጋር ማደሪያው ማረሚያ ቤት ይሆናል፡፡

## 8. በስልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራ ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ በቀረበው ተሰሚነቱ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የስራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት የአገልግሎት ዋጋ ልዩ ችሮታ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት (እኔ አስጨርስልሃለሁ እንደማለት) ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡

## 9. በሕገ-ወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ በሕግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ ግብር ልዩ ልዩ ገቢ ጥቅም ምንዳ፣ ደሞዝ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆን የማንኛውንም ዕቃ ወይም በሚያስረክብበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ሲከፍል ወይም ሲያስረክብ የሙስና ወንጀል ሕጉን ተላልፏል እና ለፍርድ ይቀርባል፡፡

(በሚቀጥለው ወር ዕትም ይቀጥላል)

# ኪነ-ጥበብ

## ሥነምግባር ግጥም

## ‹‹ሠልጥነናል ኮ!››



የአፋሯ እመቤት፣ የእማ ሉሲ ዘሮች፣
የልጅ ልጅ፣ ልጅ፣ ልጅ፣ ልጅ፣ ልጆች፤
የጎቦድራን ዓለት እንደወርቅ አንጥረው፣
ሮሐን በርብረው፣
እንደ ቅኔ አርበኛ ድንጋዩን መሥጥረው፤
ጀጎልን፣ ፋሲልን፣ ጢያን፣ ቱቱፈላን በጥበብ አናግረው፤
አስረክበውናል የሠለጠነ ሀገር፣ ትልቅ ምድር ፈጥረው።
እኛም እንደእነሱ በጥበብ ልቀናል፤ አዎ ሠልጥነናል፤
ጀሰውን ጤፍ አርገን መብላት ጀምረናል።
ቀይ አሸዋ ፈጭተን በርበሬ ፈጥረናል፤
ሙዙን በምርምር ቅቤ አድርገነዋል፤
ከወዳደቀ ቁስ፣ ከርጋጭ፣ ብስባሽ፣ ዘይት አምርተናል፤
ስኳሩን ቀምመን ማር አድርገነዋል፤ንብን ተክተናል፤
አዎ ሠልጥነናል!
በምግባር ልቀናል፤ ኧረ አልፈን ሄደናል።
ሠልጥነናልኮ!
በተማርነው ትምህርት፣ ባገኘነው ዘዴ፣
አረማመዳችን ተቀይሯል በአንዴ፤
እግራችንን ንቀን በእጃችን መዳዝን ለምደነው የለ እንዴ!?
ሠልጥነናልኮ!
እነ ላሊበላ ከሺህ ዓመት በፊት የጠረቡት ድንጋይ፣
‹‹ዘባ›› የማይለው ሲፈራረቁበት ዝናብና ፀሐይ፣
ጊዜ ስለጣለው፣ ስለወደቀነው ኋላቀር እጆች ላይ።
ዛሬ ግን...
የገነባነው ፎቅ፣ የሠራነው ድልድይ፣ ፈጥኖ ካልተናደ፣
ምኑን ተራቀቅነው?ጥበብ እንዴት ይደግ? ድካም፣ ልፋታችን ምኑን ተራመደ?
ፋሽኑ ሲያልፍበት ቶሎ ካልፈረሰ፣ ካልተደረመሰ፣
እንደ ላሊበላ ተገትሮ ቢኖር ያስተማረን ‹‹ምሁር›› መች አንጀቱ ራሰ?
ሠልጥነናልኮ!
እንደ ትናቱ አይደል ጥበባችን መጥቋል፤
ረቅቋል፤ ተራቅቋል፤
እንቅርት ልታስወጣ ከሆስፒታላችን የተኛችውን ሴት፣
ኩላቷን ቀድደን መልሰን ሰፍተን ነው ፈውስ ያስገኘንላት፤
በእኛ ዘመንኮ እኛኑ ይመስል በሽታም ሠልጥኗል፤
አንገት ላይ መውጣቱን እርግፍ አርጎ ትቶ፤ እንቅርት የሚገኘው ...ኩላሊት ላይ ሆኗል።
ጋንግሪን ወጥቶበት እግሩን ለመታከም ማንም ሰው ሲመጣ፤
አንገቱን ብንቆርጠው ወዲያው ፈውስ ያገኛል፤ ምንም የለው ጣጣ።
ሠልጥነናልኮ!
ተማሪ ሰብስበን፣ ምድረ ውሪ ከብበን ማስተማር ላይ ሳለን፣
የለመድነው ልማድ ድንገት ትዝ ሲለን፣
በሩን እንደዘጋን በመስኮቱ ዘልለን፣
‹‹ንካው!›› ብንባባል ‹‹ብንነካው›› ምን ይላል?
እውቀት እንደሆነ በየሱቁ ሞልቷል፤
ተራ ሸቀጥ ሆኗል፤ ገንዘብ ያለው ሁሉ ሄዶ ይሸምታል፤
እንደ ቅኔ መምህር፣ ወይ እንደ ደረሳ ቀን ሙሉ ማስተማር እውቀት ያባክናል።
ቀድሞ ነገር ተሜ ትምህርቱን ለማጥናት ለምን ይጨነቃል?
ዕውቀት በየጎሬው እንደ ውኃ ይፈልቃል።
ሠልጥነናልኮ!
እሱ ተበድሎ፣
ቤተሰቡ ቆስሎ፤ ሌላኛው ወገኑ በዓመፅ ተገድሎ፣
ማስረጃ ሰብስቦ በመጣ ከሳሽ ላይ ፍርድ ካልተሰጠ፣
በሐብት አጠብ ድሎ በቆንጆዎች ጀርባ ካላስፈናጠጠ፤
ጎሊናን በገንዘብ ፈጥኖ ካልሸቀጠ፤
ፍትሕ ምን ያረጋል ድሃን እንደ ጌሾ በደንብ ‹‹ካልወቀጠ?››
ዳኝነት ምንድን ነው ኪስ ካላሳበጠ?
ሠልጥነናልኮ!
ሰው ማክበር፣ ደግነት፣ ለተራ በማብላት ምን ይሠራልናል?
ኋላቀር አሳብ ነው፤እኛ ሠልጥነናል፤
ብቻችንን ኖረን ለየብቻ መሞት እሱው ይሻለናል፤
አቦ ሠልጥነናል።
ማንኛውም ዜጋ ባለ ጉዳይ ሆኖ ቢሯችን ሲመጣ፣
ከጉዳዩ በፊት ‹‹ፍሉስ›› ካላሳየ እጅ እግሩ ከነጣ፣
መጀመሪያውንስ ከደሳሳ ጎጆው ከቤት ለምን ወጣ?
ጣጣ!!
ሰልጥነናልኮ! ጉዳይ ማሳለጫ፣ መቅቡጥ ካላመጣ፣
ፊርማችን አያምርም፤ ኧረ መጀመሪያም ብዕር ከኪሳችን ‹‹እሽ›› ብሎ አይወጣ።
እንደ ጥንት አባቶች፣ ኋላ እንደ ቀሩቱ፣
ድንጋይ ተንተርሰው፣ ጤዛውንም ልሰው ኑሮ እንደገፉቱ፤
እንዲያው ለወግ ያህል ‹‹አትስረቅ›› ብንልም፣
ትክክል አይደለም፤
ሠርቶም ሆነ ሰርቆ ማደግ ከተቻለ፣ ካልተከለከለ፣
ሠልጥነናልኮ ብንሰርቅስ ምን አለ?
ሠልጥነናልኮ!
ባገኘነው ዕውቀት፣ በሸመትነው ጥበብ፣
ጋዜጣ ላይ ብንጽፍ፣ ደስያለንን ወሬ ቢያሻን በራዲዮ በቲቪ ብናነብ፣
‹‹ዩቱብ›› በሚባለው፤የደበረንን ሰው ብንውል ስንሳደብ፣
ያልሞተውን ገድለን፣ መርዶ ብናወራ፣ ወሬ ብናራግብ፣
ብሄርን ከብሄር፣ አማኝን ከእምነቱ፣
አፍቃሪን ከፍቅሩ፣ ደጉን አባዎራ ከሚወዳት ሚስቱ፤
መሪና ተመሪን፣ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ተግቶ ማራኮቱ፤
ብር ካስገኘልን ምንድን ነው ጥፋቱ?
ሠልጥነናልኮ!
ሰው እንደ እንጨት ቢነድ፣ ባገሩ ቢሰደድ፣
ቢወርድ፣ ቢዋረድ፤
እኛ ሊቃውንቱ መመራመር እንጂ ሌላ ምን አለ ንግድ?
እንመረምርና፣ እንጠበብና፣
‹‹በጥይት በረዶ?በገጀራ ታርዶ፣ በነዳድ ሲቃጠል?
ወይስ...
መሃል ደረቱ ላይ መርዝ በተቀባ፣ሹል ቀስት ቢነደል?
የቱ ነው የሚሻል?
ጥሩ ሞት የሚሞት፣በምን ቢገደል ነው?ምድር የምትሆን ሲያል?››
ብለን ተመራምረን፣ ከመሰል ሊቃውንት በሐሳብ ተፋትገን፣
ስለ መቃብሩ መፍትሔ እንሰጣለን ለቀባሪ ወገን።
ሠልጥነናልኮ!
ኧረ ሠልጥነናል!
ጥያቄ ግን አለኝ፤
ሁላችን አብደናል፤ ‹‹ጨዋ›› እሚባል ጠፍቷል፤
መልካም ሥነምግባር ከሀገር ሊሰደድ፣ ጓዙን አሰናድቷል፤
እህስ......?
አብረን እንሰደድ?
ወይስ ከጀመርነው ወልገድጋዳ መንገድ፣
እንመለስና ብቸኛ ሀብታችን እማማ ኢትዮጵያን ፈጥነን እንታደግ?
ሠልጥነናልኮ!

በአቶ አበረ አዳሙ
(ግንቦት 16/2013 በሸራተን አዲስ 20ኛ ዓመት
የኮሚሽኑ የምስረታ በዓል ሲከበር የቀረበ ግጥም)

## መልካም ዜጋ

# የብሄራዊ ትስስር/ቅንጅት ስርአት (National Integrity System) ሙስናን በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ

በአንድ አገር የመንግስት አሰራርን ለማከናወን የተዋቀሩ ተቋማት ሚዲያ፣ የፍትህ፣ የዲሞክራቲክ ፣ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት .... ጠንካራ በማይሆኑበት ጊዜ ሙስና የየእለት የዜጎች ፈተና ይሆናል፡፡ አንዱ ተቋም ጠንካራ ሆኖ ሌላው ደካማ በሚሆንበት ጊዜም ጠንካራው በጥንካሬው ልክ ሙስናን እንዳይታገል ደካማው ተቋም ደግሞ ማነቆ ወይም እንቅፋት ይሆንበታል፡፡ ተቋማት የተገነቡበት አደረጃጀት ደካማ ከሆነ ሌብነት ወይም ሙስና ጉልበተኛ ሆኖ በአደባባይ ሲንጎራደድ ማንም ሃይ የማለት አቅም አይኖረውም፡፡


እ.ኤ.አ በ1960 እና 70 አካባቢ ሆንግ ኮንግ እጅግ በጣም ሙስና የተንሰራፋባት ሃገር ነበረች፡፡ ሙስና ከመስፋፋቱ የተነሳ የሰዎች የእለት ከዕለት ህይወት አካል እስኪመስል ድረስ ነበር፡፡ የነበረውን የሙስና ጥልቀት ለመግለጽ ዘይቤያዊ በሆነ አነጋገር “ሙስና ከውልደት እስከ ሞት” “from womb to tomb”. ይባልለት ነበር፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ በሚካሄድባቸው በህግ አስፈጻሚዎች አካባቢ የተደራጀ ሙስና ከሚፈጸምባቸው አካባቢዎች የሚጠቀሱ ነበሩ፡፡ ሙስናው አይን ያፈጠጠ እንደነበር ከሚያረጋግጡት መገለጫዎች መካከል ሙሰኛ የትራፊክ ፖሊሶች ለታክሲ አሽከርካሪዎች የሚሰጡት ስቲከር ነበር፤ ይህ ስቲከር ታክሲ አሽከርካሪዎች ለትራፊክ ጉቦ እንደከፈሉ ማረጋገጫ የሚሆን ነበር፡፡ አሽከርካሪው ያን ስቲከር ታክሲው ላይ ይለጥፋል፤ ከዚያም ለአንድ ወር ያህል ከማንኛዉም የትራፊክ ወንጀል ነጻ ይሆን ነበር፡፡ ይሁንና በሆንግ ኮንግ ገለልተኛ የሆነው የጸረ-ሙስና ተቋም በተቋቋመ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ እንደዚህ ፈጠው የወጡት የሙስና መገለጫዎች በሙሉ ተወግደዋል፡፡ አሁን በአለም ላይ ሙስና በዝቅተኛ ደረጃ ከሚፈጸምባቸው አገራት መካከል አንዷ ሆንግ ኮንግ ናት፡፡

ሙስና እንዲህ እየከፋ በሚሄድበት ጊዜ የሃገር ዘላቂ ልማት፣ የህግ የበላይነት እንዲሁም የዜጎች ሰላማዊና የተሻለ ኑሮ አደጋ ላይ ይወድቃሉ፡፡ በመጨረሻም አገር ብሄራዊ አንድነቱን ጠብቆ እንደሃገር የመቀጠሉ ሁኔታ ፈተና ውስጥ ይገባል፡፡ በመሆነም ሙስና እንዲህ የከፋ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ በመንግስት አሰራር ውስጥ ያሉ ተቋማት ሙስናን ለመከላከል ጠንካራ ተቋማት ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትስስር ሊሰሩ ይገባቸዋል፡፡ በየተቋሙ የሚወጡ ህጎችና ደንቦች ሙስናን በመከላከል ረገድ ለራሳቸውም ሆነ ለሌላው ተቋም የጥንካሬ ምንጭ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ሙስና በአንድ ተቋም ውስጥ ብቻ የሚታይ ወንጀል እንዳልሆነ ሁሉ በአንድ ተቋም ብቻም መከላከል አይቻልም፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሚፈጸም የሙስና ተግባር ሌላውንም ተቋም ይጎዳል፤ ባንጻሩም ሙስናን በመከላከል ረገድ የአንድ ተቋም ጥንካሬ ለሌላውም ብርታት ይሆነዋል፡፡ አለምአቀፉ ተቋም ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ሙስናን በብሄራዊ ደረጃ ለመከላከል ተቋማት በቅንጅትና በትስስር መስራት ያስችላቸው ዘንድ የብሔራዊ ትስስር ስርአትን (National Integrity System) አስተዋውቀዋል፡፡


### የብሔራዊ ትስስር ስርአት ምንድን ነው?

የብሔራዊ ትስስር ስርአትን በቀላሉ ለመገንዘብ ጥንታዊውን የግሪክ ቤተመቅደስን ማስተዋል የግድ ይላል፡፡



የጥንታዊ የግሪክ ቤተመቅደስ

በምስሉ ላይ እንደሚታየው ህንጻውን ያቆሙ በርካታ አምዶች ተደርድረዋል፡፡ የግሪክ ቤተመቅደስ ህንጻ የተዋቀሩበት አምዶች እጅግ ጠንካራ ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳም አንዳንዶቹ አምዶች ዛሬም ድረስ ቀጥ ብለው ይገኛሉ፡፡ እናም ይኸው አሁን ከሁለት ሺህ አመት በኋላ የብዙ ቱሪስቶችን ቀልብ ስበው ይገኛሉ፤ ይጎበኛሉም፡፡ ህንጻው የተገነባበት መሰረት ጠንካራ መሆን የጣራውን ድምድማት የተሸከሙት አምዶች ጥንካሬ በውበቱና በጽናቱ ዓመታትን እንዲሻገር አድርገውታል፡፡ ከዚህ በታች ያለው ምስል ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የግሪክ ቤተመቅደስ የህንጻ ውቅርን መሰረት በማድረግ ሙስናን ለመከላከል ተመራጭ ስልት የሆነውን የብሔራዊ ትስስር ስርአትን ለማስገንዘብ ያቀረበው ምስል ነው፡፡




በምስሉ ላይ እንደሚታየው ህንጻው ሁለት ደረጃዎች ያሉት ጠንካራ መሰረቶች አሉት፡፡ የህንጻውን ድምድማት የተሸከሙ ልዩ ልዩ አምዶች ይታያሉ፡፡ አምዶቹ እርስ በርሳቸው ተሳስረው የህንጻው ጣራ ውሃ ልኩን ጠብቆ በላዩ ላይ ያሉትን ጉልላቶች ተሸክሞ እንዲቆይ አስችሎታል፡፡ እንግዲህ ከስዕሉ መገንዘብ እንደሚቻለው ቤተመቅደሱ እንደ አንድ ህንጻ የተሟላ ሆኖ እንዲቆም ቤቱን የመሰረቱት ግብአቶች ጥራትና ጥንካሬ እንዲሁም ትስስር ወሳኝ ናቸው፡፡ የህንጻውን ልዩ ልዩ ክፍሎች ነጣጥለን በማየት ሙስናን ለመከላከል ያላቸውን አንድምታ እንቃኛለን፡፡

የህንጻን ጥንካሬና ጥራት ለማወቅ አስቀድሞ ስለመሰረት ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ የመሰረት ጥራት የህንጻውን ጥራት እና እድሜ ይወስናል፡፡ በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነቡ ህንጻዎች ለረጅም ጊዜ ጥንካሬያቸውን ጠብቀው የሚፈለግባቸውን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ መሰረቱን ጠለቅ አድርጎ የቆፈረና ተገቢውን ግብአት ተጠቅሞ ህንጻውን ያዋቀረ መሃንዲስ ለህንጻው ጥንካሬ ዋስትና መስጠት አያዳግተውም፡፡ ከዚህ አኳያ በምስሉ ላይ እንደሚታየው ተቋማቱ የተገነቡት በህብረተሰቡ ግንዛቤ (public awareness) እና በህብረተሰቡ እሴቶችና ልማዶች (society’s values) ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የህዝብ ንቃተ ህሊና ማደግ እንዲሁም የሚመራባቸው የሞራል እሴቶች ጠንካራ መሆናቸው የቆሙትን አምዶች ጠንክረው እንዲቆሙ ያደርጋል፡፡ ዜጎች ሙስና በሚያስከትለው ጉዳት ላይ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው ከሆነና ጉቦ ሲጠየቁ “ለምን?” ብለው የማይጠይቁ ከሆነ የህዝብ ሃብት ሲዘረፍ የማይቆረቆሩ ከሆነ፣ የሚፈጸሙ ችግሮችን ነቅተው የማይጠብቁ፣ የማይጠቁሙ ከሆነ፣ እንዲሁም ሙስናን የሚጸየፍ እሴት ካላዳበሩ ተቋማቱ የቆሙበት አስተማማኝ ባልሆነ መሰረት ላይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የጸረ-ሙስና ትግል ደግሞ ያለህብረተሰብ ተሳትፎ ግቡን አይመታም፡፡ ታክስ ላለመክፈል ጉቦ መክፈልን እንደ ትክክለኛ አማራጭ ቆጥሮ የሚጠቀም ህብረተሰብ ባለበት አገር ውስጥ ሙስናን መታገል ከባድ ነው፡፡

በሌላ በኩልም በእያንዳንዱ ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች ከህብረተሰቡ የሚወጡ በመሆኑ ጠንካራ እሴት ከሌለው ማህበረሰብ ውስጥ የሚወጡ ሰዎች በተቋማት ውስጥ ገብተው ጠንካራ ስራ ይሰራሉ ማለት ያዳግታል፡፡

በመሆኑም ሙስናን በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡ ጽኑ መሰረት እንዲኖረው ልዩ ልዩ ስልቶችን በመጠቀም ንቃተ ህሊናው ማደበር ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊና ከፍ ለማድረግ በሌብነት/በሙስና አስከፊነትና በሚያስከትለው ጉዳት ዙሪያ፣ ህብረተሰቡ ጉቦ ሳይከፍል አገልግሎት ማግኘት መብት እንዳለው፣ አገልግሎት ማግኘት ፈልጎ ሲሄድ ለሙስና የሚገፋፋ አዝማሚያ ሲያጋጥመው እንዴት ማጋለጥ እንደሚችል የግንዛቤ ስልጠና ሊሰጠው ይገባል፡፡ ወጣቶችም በጠንካራ እሴቶች የተገነቡ ሆነው እንዲያድጉ የወጣቶችን ስብእና በመገንባት ዙሪያ ተልእኮ ያላቸው ተቋማት ትልቅ ስራ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ ወጣቶች ወደፊት በእያንዳንዱ አምድ(ተቋማት) ውስጥ ስራ ለመስራት ሲገቡ ወይም ሲቀጠሩ በገነቡት ጠንካራ እሴት አማካኝነት ብሔራዊ ትስስሩን አጽንተው በመጠበቅ ረገድ ሚናቸው የጎላ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ትውልድን በሥነ-ምግባር ማጎልበት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በምስሉ ላይ ከመሰረቱ ቀጥሎ የሚታዩት የህንጻውን ድምድማት የተሸከሙት አምዶች ናቸው፡፡ እነዚህ አምዶች በመንግስት አሰራር ውስጥ ያሉ ተቋማትን የሚወክሉ ናቸው፡፡ አምዶቹ እርስ በርስ የተሳሳሩ ናቸው፡፡ የመንግስት ተቋማትም እንዲሁ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተቋማቱ በተናጠል ያላቸው ጥንካሬና ድክመት ለሌላው ጥንካሬ ወይም ድክመት ምክንያት ይሆናል፡፡ አንዱ አምድ ደካማ ከሆነ ቤቱን የመሸከም ጫናው ወደሌሎቹ አምዶች ይሸጋገራል፡፡ ሙስናን ለመከላከል ሁሉም ተቋማት ብርቱ ካልሆኑ ሙስናን የመታገል ጫናው በአንድ ወይም በተወሰኑ ተቋማት ጫንቃ ላይ ይወድቃል፡፡ ይህ ደግሞ ሙስናን በመከላከል ብዙ ርቀት አያስኬድም፡፡ የአምዶቹ ጥንካሬ ህንጻው ለረጅም ጊዜ እንዲቆም ከዚህ የተነሳም በህንጻው አናት ላይ ያሉት ጉልላቶች ወይም ድቡልቡል ኳሶች እነሱም (ዘላቂ ልማት፣ የህግ የበላይነት፣ ጥራት ያለው ኑሮ) ሳይወድቁ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቆዩ ያደርጋል፡፡ በአንጻሩም የአንዱ ወይም የሌላው አምድ ድካም ቤቱ እንዲዘምና ጉልላቶቹ ወይም ኳሶቹ እንዲወድቁ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ዘላቂ ልማት፣ የህግ የበላይነት እንዲሁም ጥራት ያለው ኑሮ አደጋ ላይ መውደቃቸውን ያመለክታል፡፡ በመጨረሻም ከነ አካቴው ቤቱ ሊፈርስ ይችላል፡፡

አምዶቹ ወይም ተቋማቱ የተዋቀሩበትን ግብአት ስናስብ በተቋማት ውስጥ ያሉ በጠንካራ መሰረት ላይ የታነጹ ሰራተኞችን፣ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚገቡ አዋጆች፣ ደንቦች( rules) እና የአሰራር ስርአት (practices) አብረው ይታሰባሉ፡፡ ለዚህ ነው ሙስናን ለመታገል የተቋማት ግንባታ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው፡፡ ከዚ ቀጥሎ ሙስናን በመከላከል የአንዱ ተቋም ጥንካሬ ወይም ድካም በሌላው ተቋም ላይ እንዴት ተጽእኖ ሊያስከትል እንደሚችል አንዳንድ ምሳሌ እያነሳን እንመልከት፡፡

በፍትህ ስርአት ውስጥ ያሉ ተቋማት ነጻና ገለልተኛ ሆነው በተጠያቂነት መንፈስ ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ከሆነ የተዋቀሩበት ምሶሶ የጠነከረ ስለሚሆን ቤቱ በጥንካሪው የሚጸና ይሆናል፡፡ ይሁንና የፍትህ ስርአቱ ገለልተኛ ካልሆነ፣ የተጠያቂነት ስርአቱ የላላና በሙስና የተጠላለፈ ከሆነ የቤቱ አንዱ ምሶሶ ተናጋ ማለት ነው፡፡ በሌሎች ተቋማት ውስጥ ያሉ ሙሰኞች እንደፈለጉ እንዲፈነጩ እድል ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ሌሎች የተዋቀሩበት ምሶሶ በብል እንደተበላ እንጨት መውደቁን የሚጠበቅ ልፍስፍስ ምሶሶ ይሆናል፡፡

ሚዲያን የሚወክለው አምድ ሃሳብን በነጻ በመግለጽና መረጃ በማግኘት መብቶች ሊጠናከርና ጠንክሮ ሊቆም ይገባዋል፡፡ ሚዲያ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ሚዲያው መልካም ስነምግባርን በማስፋፋት ሙሰኞችን ተጠያቂ በማድረግ የሚሰራው ስራ ጠንካራ ከሆነ ከጎኑ ያሉ አምዶችም ተጠንቅቀው እንዲሰሩ ወይም ጠንካራ እንዲሆኑ ምክንያት ይሆናል፡፡

በሙስና የተመዘበረና ከሀገር የሸሸ ሃብትን ለማስመለስ አለም አቀፍ አጋርነትና ትብብር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ሌቦች የዘረፉትን ገንዘብ አስተማማኝ ገነት “safe havens” በሚሉበት ቦታ የዘረፉትን ገንዘብ ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህ ረገድ ድርሻ ያላቸው ተቋማት ስራቸውን በአግባቡ ካልተወጡ ሙስናን በመከላከል የሚደረገው ጥረት ፈታኝ ይሆናል፡፡

በመጨረሻም የብሔራዊ ትስስር ስርአት የመጨረሻ ግብ ሙስና ወይም ሌብነት ውስጥ ከፍተኛ አደጋ እንዳለው ወይም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን በተግባር ማመላከት ነው፡፡ በሌላ በኩል ሙስናን በመከላከል ሂደት ውስጥ አንድ ተቋም ላይ ብቻ ትኩረት ከማድረግ ሁሉም ተቋማት የየራሳቸውን ሚና እንዲወጡ በማድረግ በትብብር እና በትስስር ሙስናን በመታገል የተሻለ አቅጣጫ ማሳየት ነው፡፡ ይህ አቅጣጫ ሁለንተናዊ የትግል ስልትን (holistic approach) ስለሚከተል ሙስናን የመከላከል ስራውን ቀላል ወይም ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም የፌደራል ሥነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ዜጎች በጠንካራ መሰረት ላይ የታነጹና ሙስናን የሚጸየፉ እንዲሆኑ የስነምግባር ትምህርትን በማስፋፋት፤ ተቋማት ሙስናን በመከላከል ረገድ የሚስተዋልባቸውን ድክመት እንዲያስተካክሉ ያደረገ ሴክተር ተኮር የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት በማጥናትና መረጃን በማመንጨት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በትብብር እና በቅንጅት ለመስራት አደራጃጀቱን እንደገና በማሻሻል ወደ ስራ ገብቷል፡፡